ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

ጥር 6፤2004 ዓም

# የጋምቤላ ርዕሰ መስተዳደር የግምገማ ውጤት ተገለበጠ!

## "ሙስናን ለመዋጋት የተካሄደ ግምገማ በሙስና ተደመደመ" (ተሰብሳቢዎች)

በጋምቤላ ሲካሄድ የሰነበተው ግምገማ ከሥራ አስፈጻሚው ውሳኔ ውጪ መወሰኑ አነጋጋሪ ሆነ። በክልሉ በተለያዩ የንግድና የኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩ ባለሃብቶችና ነጋዴዎች የግምገማው ውጤት እንዲገለበጥ አስገምጋሚዎቹን ማሞዳሞዳቸው ተጠቁሟል።

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የመረጃ ምንጮች እንዳስታወቁት፣ የጋምቤላ ሕዝቦች አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ጋሕአዴን/ ከፌደራል ኢህአዴግ ፅህፈት ቤት በተላኩት አቶ ዘመዴ ዘመድኩንና አቶ አለባቸው ንጉሤ አማካይነት ከታህሳስ 17 ቀን 2004 ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው ድርጅታዊ ግምገማ አጀማመሩ ጥሩ ነበር።

ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ የጋሕአዴን አባል ለጋራ ንቅናቄያችን ሲያስረዱ የፓርቲው ሥራ አስፈጻሚ የወሰነው ውሳኔ የተገለበጠው ከሙስና ጋር በተያያዘ ነው። "ተገለበጠ" ስላሉት ውሳኔ ሲያስረዱ ሙሉ በሙሉ በሥራ አስፈጻሚው የተወሰነው ወሳኔ፤ አቶ ኦሞት ኦባንግ ከፕሬዚዳንትነት መንበራቸውና ከፓርቲው ሊቀመንበርነት አሰናብቷል። አቶ ጓናር የር በተመሳሳይ ከምክትል ፕሬዚዳንትነትና ከፓርቲው ኃላፊነታቸው ያገለለ ሲሆን፣ ሌሎች የከፋ የሙስናና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች አለባቸው የተባሉ ሁለት ሥራ አስፈፃሚዎች ኮር ፖዎችና ጀምሰ ዴንግ ከሥራ አስፈጻሚ እንዲወገዱ ያደረገ እንደነበር አመልክተዋል።

ባለሥልጣኑ ውሳኔው ተገልብጦ ፕሬዚዳንቱ በኃላፊነታቸው እንዲቆዩ የተደረገበትን ምክንያት ባይዘረዝሩም በደፈናው "ሙስናን ለመታገል የተካሄደ ግምገማ በትልቅ ሙስና ዋጋ እንዲያጣ ሆነ። ችግር እንዳይከሰት ስጋት አለኝ" የሚል መልስ ሰጥተዋል።

ለጋራ ንቅናቄያችን ስም ዝርዝር አካቶ ከስፍራው የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው አስገምጋሚዎቹን ለመደለልና ፕሬዚዳንቱን ለመከላከል በክልሉ ሰፋፊ መሬት ያላቸው ባለሃብቶችና ነጋዴዎች ስብሰባ በማካሄድ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ አሰባስበዋል። ባለሃብቶቹንና ነጋዴዎቹን በማስተባበርና መዋጮውን በማሰባሰብ ሥራ ላይ ከማዕከል ፕሬዚዳንቱን እንዲያማክሩ የተላኩት አቶ ብሌን ከፍተኛውን ሚና ተጫውተዋል።

ሙሉ በሙሉ በጥፋተኛነት ተፈርጀው እስር እንደሚጠብቃቸው የተገለጸላቸው አቶ ኦሞት ኦባንግ የፕሬዚዳንትነት መንበራቸውን እንደያዙ እንዲቀጥሉ ይፋ ሲደረግ ከወረዳ የመጡ የበታች አመራሮችን ጨምሮ በመሰብሰቢያ አዳራሹ ውስጥ ከፍተኛ ተቃውሞ ተሰንዝሮ ነበር።

በግምገማው የተሳተፉ የፓርቲው አባላት በወቅቱ ስለነበረው ተቃውሞ ያስረዱን "ሰው የማይወደው፣ የሥራ አፈጻጸም ችግር ያለበት፣ ለሰላምና ለጸጥታ ችግር የሆነ፣ በሙስና የተጠመቀ፣ በተለያዩ ወንጀሎች የሚጠየቅ ሰው በኃላፊነት ማስቀጠል አግባብ አይደለም። ችግርም ያስከትላል . . ." በሚል በእልህ የሚናገሩ ነበሩ። ይሁን እንጂ አቶ ኦሞትን በኃላፊነት ለማስቀጠል አስቀድሞ የተወሰነ ስለነበር የተሰጠው ምላሽ ማስፈራሪያና ማሸማቀቂያ ነበር።

በግምገማው መጀመሪያ ጭንቀት ውስጥ የነበሩት አቶ ኦሞት የግምገማው ውጤት መገልበጡን ካረጋገጡ በኋላ ስልክ በመደወል ምክትላቸው አቶ ጓነር ከኃላፊነታቸው እንደሚነሱ በመጥቀስ የተቃወሟቸውን እንደሚበቀሉ ማስጠንቀቃቸውን የድርጅታችን ምንጮች አስታውቀዋል። አያይዘውም ውሳኔውን ለማስገልበጥ በአቶ ብሌን አማካይነት ገንዘብ ሲያሰባስቡ ከነበሩት መካከል አቶ ሸዋየ ብሩ የንግዱ ማኅበረሰብ ሰብሳቢ፣ አቶ ሰይድ ነጋሽ በክልሉ በኮንስትራክሽን ስራ የተሰማሩና የአቶ ኦሞት ኦባንግ ታማኝ ወዳጅ፣ አቶ ታደሠ ኃይለሥላሴ የአቶ ኦሞት ኦባንግ የደኅንነት ኃላፊና በአኙዋክ ንጹሃን ዜጎች ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ ሲካሄድ

ዋና ተዋናይ እንደነበሩ የሚመሰከርባቸውና በወቅቱ የጋምቤላ ፖሊስ አዛዥ፣ አቶ ያሲን በላይ የክልሉ መስተዳድር ጽህፈት ቤት ባለሙያ፣ አቶ ደሳለኝ ብሩ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ተወካይ፣ አቶ መስፍን ገዛኸኝ የክልሉ የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፣ አቶ ሲሳይ ተስፋዬ ከፋክት ኢትዮጵያ ሎጂስቲክስና የአቶ ኦሞት የቅርብ ወዳጅና ሌሎችም በሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር በማሰባሰብ ስራ ከተሰማሩት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። በሌላ በኩልም የኢትዮጲስ ኮሌጅ ባለቤትና ፕሬዚዳንት አቶ አዲል አብደላና አቶ ታየ አርሲ የተባሉ ግለሰቦች በሙስናው ውስጥ እጃቸው እንዳለበት የደረሰን መረጃ ጠቁሟል፡፡

የስም ዝርዝራቸውን ያካተተውና ለውሳኔ ማስገልበጫ የተሰበሰበውን 3ሚሊዮን ብር ምንጭ ጠቅሶ የተላከልን መረጃ እንደሚለው በክልሉ የተሰማሩ ከፍተኛ ኢንቬስተሮች ባላቸው የግንኙነት መስመር ገንዘቡ ለአስገምጋሚዎቹ እንዲደርስ በማድረግ ፕሬዚዳንቱ በኃላፊነታቸው እንዲቆዩ ተጽዕኖ ማድረጋቸውን ይጠቁማል።

በቀጣይ ስድስት ወራት መሻሻል እንዲያሳዩ ተመክረው መንበራቸው ላይ የተቀመጡት አቶ ኦሞት፣ በቀጣይ የበቀል ርምጃ ለመውሰድ የተመቻቸላቸውን አጋጣሚ እንደሚጠቀሙበት ስጋት የገባቸው ጥቂት አይደሉም። ግምገማው ውድቅ መሆኑና የሥራ አስፈጻሚው ውሳኔ መገልበጡን ካረጋገጡ በኋላ ዛቻ የጀመሩት ፕሬዚዳንቱ "የማጥራት ስራ እጀምራለሁ" ማለታቸው ታውቋል።

በጋምቤላ ሙስና በከፍተኛ ደረጃ እንደሚገለጽ፣ ልማት የተጓተተ እንደሆነ፣ መልካም አስተዳደር ከጊዜ ወደጊዜ እየባሰበት መሄዱን፣ የክልሉ ሰላም አሳሳቢ መሆኑና በአኙዋክ ንጹሃን ወገኖች ላይ የተካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋ ፕሬዚዳንቱን ዋጋ ያሳጡና በወንጀል ሊያስጠይቁ እንደሚገባ ባለፈው ሳምንት በክልሉ ያሉትን ምንጮች በመጥቀስ መዘገባችን አይዘነጋም። በዘገባው ከዘጠኝ ዓመት በፊት ስለተፈጸመው የወገኖቻችን እልቂት ተጠያቂ የተደረጉት ፕሬዚዳንቱ "እኔ ከታሰርኩ ወታደርና መሳሪያ የሰጡኝ አቶ መለስም ይታሰራሉ ማለታቸው ይታወሳል"፡፡

አቶ ኦሞትን በመተካት የጋህአዴን ሊቀመንበር ሆነው የተሾሙት አቶ ጋትሎክ ኮት ሲሆኑ አቶ ኦሞት የተነጠቁትን የፕሬዚዳንት መንበር በወዳጆቻቸውና በቀኞቻቸው ጥረት መልሰው በመረከብ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት ይቀጥላሉ። አስተያየት ሰጪው እንዳሉት "ከክልሉ የሚሰበሰብ ኃብት መልሶ ለክልሉ ጠላት እየሆነ ነው። እንደኔ እምነት አሁን የተፈጠረው ችግር በቀላሉ የሚቆም አይሆንም። ቀጣዩን ችግር በገንዘብ ሃይል ማቆም አይቻልም"፡፡

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለዋና ዳይሬክተሩን አቶ ኦባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመነብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

